# ሐገራዊ እርቅ

(National Reconciliation)

ካንዳንድ የተዛቡ አስተያየቶች ውስጥ

በገጠመን ሐገራዊና ሕዝባዊ ብኽርታ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን ከገባንበት አዘቅት ለመውጣት ፣ በብረት ኃይል ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ብሎ በሕዝባችን ሀብትና ንብረት መበለጉ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን ልምድና ባህል በማግማማት የሕብረተሰቡን የአንድነት ድርና ማግ በመበጣጠስ የፖለቲካ ህልውናውን በማሳጣት ኢትዮጵያ የምንለው ክቡር የአንድነት ማንፈሳችንን ለመግደል ጥንሥሡን ሥራ ላይ አውሎ ተግባሩን ማከናወን ከጀመረ ከ15 ዓመት በላይ እንደሆነው ለማንም ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም የወያኔ መንግሥት ገሀድ ያደረገው የማይታበል ሀቅ ነው። በህገ መንግሥት መደንገጉ ብቻ ሳይሆን በእለት ተእለት በትምህርት ፣ በኢኮኖሚና በመሳሰሉት ተግባሮቹ ሲተረጉመው ማየት አዳጋች አይደለም ፣ ኢትዮጵያን ለመበተን በተባበሩት መንግስታት ሽንጎ ስለ ኤርትራ ነፃነት ከኤርትራውያን የበለጠ ታግሏል ፣ መንግሥታትንም አስገርሟል ፣ ባድሜን ለመስጠት ዋናው መስካሪ የወያኔ (TPLF) መንግሥት እንደሆነ የምንረሳው አይደለም ። እንዲያውም በቅርቡ ባድሜን በፈቃደኝነት ለኤርትራ የማስረከቡ ተግባር እንደሚፈፀም ለተባበሩት መንግሥታት ደብዳቤ በመፃፍ ግልጽ አድርጓል ።

ያለው መንግሥት ሐገሬ ድንበሬ ነው ብሎ በሚገዛት ክልል ውስጥ ጸረ ዲሞክራሲና አምባገነን ብቻ ቢሆን ኖሮ ለሕዝባዊና ለዲሞክራሲያዊ መንግሥት ምስረታ መታገሉ ትግሉን ቀላል ባያደርገውም ያለውን መንግሥት በኢትዮጵያዊነቱ የማንጠራጠረውና የሐገራችን ህልውና ያሰጋል ብለን አሁን እንደምንሰጋው ሁኔታው አጠያያቂም ባልሆነም ነበር ።

ስለሆነም አሁን ከፊታችን ተደቅኖ ያለው ችግር እጥፍ ድርብ (Multi Dimensional) እና የተወሳሰበ ሆኗል።

ወያኔ በተጨማሪ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ አንድነት በመሆኑ ይህን ተግባሩን እሙን ለማድረግ ማለትም ኢትዮጵያን ለመበታተንና አንድነቷን ለማክሰም ሲነሳ መሠረታዊ የሆነ ፀረ ሕዝባዊ እርምጃዎችን በዲሞክራሲ ስም ይዞ በመቅረብ የብሄሮችን መገንጠል በህገ መንግሥት ማወጅ በሕዝቦች ነፃነትና መብት ስም ሕዝቦች እንዲቃቃሩ አንዱ በሌላው ላይ የማይነቀል ጥላቻ እንዲይዝ ማድረግ ፣ አንዱን ሀይማኖት በሌላው ሀይማኖት ላይ እንዲነሳና የበቀል እርምጃ እንዲወስድ ማበረታታት ፣ የኢትዮጵያን የቆየና የተረጋገጠ ጥንታዊ ታሪክ ለማኮላሸትና ለአዲሱ ትውልድ የውሸት ወያኔ ዘራሽ ታሪክ በማሳተም የኢትዮጵያን የ3000 ዓመት ታሪክ በጠቅላላ በማጥፋትና ቅርሶችንም በመነገድ ሐገሪቷን ታሪክ የለሽ ማድረግ ፣ የትምህርት ተቋሙ አንድን ብሄር የተማረ ሌላውን ለትውልድ በሚያሳዝን ደረጃ ደንቆሮና ያልተማረ ፣ በጅምሩ የቀረ ትውልድ ለማድረግና ሥራ አጥ ቦዘኔ እንዲሆን በወያኔ ድርጎ ሰግዶ የሚኖር ዜጋ ለመፍጠርና እየፈጠረም ያለ መሆኑ አከራካሪ አይደለም ። በየቦታው በወያኔ አምሳል የፈጠራቸው አምሳለ ወያኔ ትንንሽ ድርጅቶች በየጎራው እንደአሸን እንደፈሉና ከኢትዮጵያዊነታቸው ይልቅ ጎጥና ደብራዊነታቸው ይበልጥ እንዲወዱና እንዲጨነቁ ከታላቋ ኢትዮጵያ ይልቅ ጠባቧን ደብራቸውን አቅፈው እንዲመለከቱ በውድ ካልሆነ በግድ በታላቁ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ላይ ተያይዞት ያለው የብተና ተግባር የበለጠ እንደተረጋገጠ በቅርቡ የትዕቢተኛው የወያኔ አባልና ምሠሦ ስብሃት ነጋ የሰጠው ቃለ መጠይቅ አከራካሪ

ካለመሆኑም በላይ በወያኔ ላይ ብዥታ ላላቸው ቅን ኢትዮጵያዊያን ታሪካዊ ምሥክርና በማሕደራችን ውስጥ ይዘን ስለወያኔ ምንነት የምናጣቅሰው ዘለዓልማዊ መረጃችን ነው ፡፡

ከዚህም አንፃር ጠለቅ ብለን በሰፊው ለማየት መጣር የብዙዎቻችን አብይ ተግባር ይሆናል ፡፡ በተለይም የትግራይ ልጆች ነን የሚሉ ምሁራን በወያኔ ሀርነት ሕዝብ ትግራይ ትግል ውስጥ ለትግራይ ሕዝብ ስንል ታገልን የሚሉ አሁን በፍጹም በወያኔ ተቃዋሚነት የተሰለፉ ፣ በኢትዮጵያዊነታቸው የማንጠረጥራቸው በሌላው በኩል የጠባብ ብሄረተኝነት ቁራኛ ያልተዋቸው በሌላው እግራቸው ደግሞ ታሪካዊ ኢትዮጵያዊነታቸውን ፈጽሞ ያልካዱና ወደ ኢትዮጵያዊነታቸውም በይበልጥ ያዘነበሉ ነገር ግን የወቅቱ ፖለቲካ ያውገረገራቸው ሌሎችም የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ስለነስብሃት መግለጫና ቀደም ሲልም ወያኔ በተለያዩ ወቅት ካሳያቸው መግለጫዎች ተግባራዊ እርምጃዎች በመነሳት “በርግጥ ወያኔ ከጽንሱ የትግራይን ሕዝብ ጥቅም ለማስከበር የተነሳ ቡድን ነበር ወይ?” የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ አንስተው መተቸት ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ ግንዛቤ ሕዝባችን ያገኝ ዘንድ የበሰሉ  ጥናቶች እንዲያደርጉና ለሕዝብ በቀላል እንደሚደርስ እንዲያደርጉ  እናሳስባለን ፡፡

የወያኔ ድርጅት ከመሰረቱ ለትግራይ ሕዝብ የተነሳ ስላልሆነ በትግራይ ሕዝብ ስም ሽፋን በማድረግ የኤርትራን ጥቅም ለማስከበር የቆመ ኤርትራዊ ድርጅት ለመሆኑ ግልጽ እየሆነ ነው ፣ ይህን መሰረታዊ ሀቅ እስካልተረዳን ጊዜ ድረስ በትግሉ ላይ የምናየው ውዥንብር ይቀጥላል ፡፡ መሠረታዊ ጥያቄዎችም እየተነሱ ይኮላሻሉ ማለት ነው ፡፡

ኢትዮጵያውያንን ኢትዮጵያዊ የሚያደርገን በአንድ በተወሰነ ክልል መስፈራችን ብቻ ሳይሆን ለብዙ ሺህ ዓመታት በጠበቀም ሆነ በላላ አስተዳደር የተለያየ ቋንቋና ባህላችን ሳይለየን ከሞላ ጎደል በየራሳችን ተከባብረን በአንድ ኢኮኖሚ ሥርአት ተሳስረን በገበያው ተዛንቀን ጠላት በመጣብን  ጊዜ ጎጥ ፣ መንደር ፣ ታቦትና መስኪድ ሳይለየን ከቆመጥ እስከ ጋሻ ፣ ከጦር እስከ ጎራዴ ፣ ሲደላም እስከ መውዜር በመታጠቅ በአንድ እዝ በአንድ ግንባር ሁነን ኢትዮጵያ ከሁሉም በላይ ታላቅ ብለን ስናስከብር ኖረናል ፡፡ ይህም ሲሆን ደግሞ ከግለሰቦች እስከ ጎጥ ክልሎች ከአንዱ ግዛት ወደ ሌላው ግዛት በመተላለፍ ከነፍስ ግድያ እስከ ሀብት ዝርፊያ ከነገሥታት እስከ ካህናት ሲጋጩ ሲፋጩ መልሰው ሲታረቁ ኑረዋል ፣ እርቅ ፣ ድርድር ፣ ሽንጎ ፣ አፈርሳታ ፣ አውጫጭኝ አጥፊን ካሽ ለበዳይ ምህረትን ለተበዳይ ካሳን በማስገኘት  ከግል ቤተሰብ እስከ መላው ኢትዮጵያዊ የሚተዳደርበትን ባህልና ወግ ጠብቀው የኖሩባት ኢትዮጵያ ሕብራዊና ልዩ የሆነው አንድነታችንና ታሪካችን ነው ኢትዮጵያዊ የሚያሰኘን ፡፡

ባሁኑ ዘመን በተለይም በ21 ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም በከፍተኛ የቴክኒዮሎጂ ስልጥኔ ባለበት ደረጃ መንግሥት የሐገሪቱን የአስተዳደር በባህልም ፣ በኤኮኖሚም ፣ በውትድርናው ማእከላዊነቱን አጠናክሮ የያዘበት ሁሉም ነገር ለማዕከላዊ መንግሥቱ የተመቻቸ በሆነበት በአንፃሩ የነበረው ሐገራዊ ትሥሥሩና የአንድነት ኃይሉ በሁሉም አቅጣጫ በተዳከመበት ወቅት ለገጠመን ችግር የውህደትና የአንድነት ኃይላችንን አጠናክረን አይበገሬ ኢትዮጵያዊ ክንዳችንን በሐገር በታኙ ወያኔ ላይ እንደማንሳት ፈንታ ከሐገር አፍራሹ ወያኔ ጋር ሐገራዊ እርቅና ሰላማዊ ጥሪ የሚል ጩኸት በየቦታው ሲነሳና ሲወድቅ ይሰማል ፡፡

ይህ ጥያቄ የወያኔ መንግሥት በብረት ኃይል መጥቶ በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ መናጠጥ ከጀመረ ወዲህ የመጣ ጥያቄ ነው ፣ ጥያቄው የብሄሮችን

እኩልነት ጥያቄ ዲሞክራሲያዊነቱን አምነው ባነሱት በቅን ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶችና ዲሞክራቲክ ኃይሎች ብሩህ የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ አስታኮ በመግባት በትግራይ ሕዝብ ስም ብዙ በሕዝቦች መካከል ደም ሲያፋስስ የማያቋርጥ ጠብ ሲጭር እናያለን ፣ በሌላው በኩል ቅን የሆኑ የብሄር እንቅስቃሴዎች በዚህ የወያኔ ተቃውሞ ላይ ተሰልፈው እናያለን ፣ የተቃዋሚ ድርጅቶችም በአንድ በኩል እራሳቸውን ሰባስበው ወያኔን ለመዋጋት ይጥራሉ ፣ ቀልበስ ብለው ወያኔንም በሐገራዊ እርቅ ሲጠይቁና ለመደራደር አብረው ለመስራት ሲማፀኑ ይታያሉ ።

ይህ የእርቅ ፍላጎትና በሰላም አብሮ መኖር ጥያቄና ድርድር ሀሳብ ምንድነው? ከየት መጣ? ለመንስ ይጠቅማል? የትስ ይወስደናል? የመሳሰሉት ጥያቄዎች አንድ በአንድ ወይም በጅምላ አንስተን መሠረታዊ ባህሪያቸውን በየበኩላቸው ካላጤንን በአሁኑ ሰዓት የተቃዋሚ ድርጅቶች ነን ባዮችና አባሎቻቸው በአጠቃላይም ወያኔን እየተቃወመ ስለብሄራዊ እርቅ የተዛባ አስተያየት ያለው አያሌ በመሆኑ ተቃዋሚ ድርጅቶችና ኃይሎች ይህን ጥያቄ በሰፊው ማብራራት ይኖርባቸዋል ። የፖለቲካ ድርጅቶች እንደመሆናቸውም በዚህ ጥያቄ ላይ ጥሩ ግንዛቤ ከሌላቸው በጠላትና በወዳጅ ላይ ተቃዋሚ ኃይሎች ያላቸው ግንዛቤ ጎልዳፋ ከመሆኑም በላይ ተቃዋሚዎች ወያኔን ከመታገል ይልቅ የተደራጀና የተጠናከረ ወያኔን ለማኘ ድርጅት ያስመስላቸዋል ፣ እስካሁን በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩት ወደዱም ጠሉም የፖለቲካ ለማኝ እንጂ የፖለቲካ ተቃዋሚ አላደረጋቸውም ። ቢይንስ ጥርስ የሌለው ውሻ ጩኸት ነው የሚያሰሙት ።

በአጠቃላይ እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሐገር በተቃዋሚውና በመንግሥቱ መካከል የሚነሱ ችግሮች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፍታት መቻል ነበረባቸው ። ነገር ግን እብሪተኛ የሆነ መንግሥት ሲያጋጥም ታግሎ ለመቀየር የዜጎች ግዴታ ስለሆነ በዚህ ትግል ውስጥ የተቃረኑ ኃይሎች ይቅር ተባብለው መሰረታዊ መፍትሄ ሊያስገኝ የሚችልበትን መሰረት ጥለው በአንድነት ያለውን መንግሥት ለማንበርከክ የግንባር ጥሪ አርገው አብሮ መሰለፍ ተገቢ ይሆናል ።

## የወያኔ መንግስት ማነው?

የወያኔ መንግሥት ሀ) ኢትዮጵያዊነቱን የማያምን ለ) በሀብት (Economy) ኃይል የደረጀ ሐ) በወታደራዊ ኃይል በጸጥታውና በሕዝብ መገናኛው የጎለበተ ኃይል ነው ። ከተቃዋሚውም ወገን እጅግ የበለጠ (Resource) ያለው ፣ ማን አለብኝ ብሎ የተቀመጠ ፀረ አንድነት ፀረ ሕዝብ ኃይል ነው ። በአንፃሩ የተቃዋሚው ወገን ያለው ኃይል ቢኖር ያልተደራጀ ሕዝብ ኃይል ነው ፣ ይህ ሕዝብ በወያኔ አገዛዝ በመንገሽገሹ የተነሳ አመቺ ጊዜ ባገኘ ቁጥር ተቃውሞውን በይፋ የሚያሳይ የመሪ ያለህ የድርጅት ያለህ እያለ የሚጮህ ሕዝብ ነው ። ተቃዋሚው ወገን በአሁኑ ወቅት ደካማ ነው ፣ ስለሆነም እርቅ የሚጠይቅና እርቅ የሚመጣው መንፈሰ ቀና ከሆነ አብሮ መኖርን ፣ አብሮ መብላትን ፣ መጠጣትን ከሚፈልግ(ጉ) በመንግስትም ደረጃ ሥልጣን ለሕዝብ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ሲገነዘብና ሲያምንም ጭምር ነው ፣ የሕዝቦችን መቀራረብ በሰላም አብሮ መኖርንና ብልጽግናን ከሚፈልግ በአንድ ገበያ መዋልን ከሐገር ሐገር ወንዝ ሳይከልላቸው እንደፍቃዳቸው ከሩቅ ሄደው ያለስጋት አንዱ ሌላውን እንደ ሌላ ሐገር ዜጋ ሳይተያዩ የሚፈቃቀዱበትን መንገድ ያየና የተረዳ ኃይል ሲሆን ብቻ ነው ። ኃይል በጁ መሆኑን አውቆ ነገር ግን የተቃዋሚው መጠናከር አስግቶት ሳይሆን ከብዕር ተዋጊው እስከ ጦር ሽማቂው ድረስ ተቃዋሚ ኃይል ጥሪ አቅርቦ "ኃይል የሕዝብ ነው" አንድ

ላይ ሁነን ፍትህ ርትዕ ያለው አስተዳደር ተማክረን እንፍጠር የሚል ኃይልና ጉልበቱን ለሕዝብ የሰጠ ኃይሌን አልጠቀምም በቃኝ ካለና መንግስቱን ለመጋራት በጎ ፈቃደኝነትን ሲያሳይ ይሆናል ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የተቃዋሚ ኃይሎች ሥልጣን ለመያዝ አንድ ሐሙስ የቀራቸው ይመስል ወያኔም ተስፋ ቆርጦ እንዳይሸፍትባቸው ሐገራዊ እርቅ ሲሉ ይሰማሉ ፡፡

- ለመሆኑ በየትኛው የተጠናከረ የተቃዋሚ ደርጅት ነው እርቁ?
- በየትኛው ድርጅት ሥር የታቀፈው ሕዝብ ኃይል?
- በየትኛው ዓለም አቀፍ ድጋፍ ጫና ነው?
- በየትኛው (Economic Resource)?
- በየትኛው ድርጅታዊ (Infiltration)?
- በየተትኛው የድርጅት ስርጭት?

በተራ አማርኛ ደካማ ድርጅት ይቅርታ እንጂ እርቅ አይጠይቅም ፣ እርቅ ስላለ ሐገራዊ እርቅ አያረገውም ፣ ይልቅስ ሐገራዊ ምህረት ጥየቃ እንጂ ፣ ደካማ የጉልበቱን ድክመት አይቶ ምህረት ወይንም ይቅርታ ይጠይቃል ፣ ኃያሉ በአንፃሩ ጉልበቱን ተመክቶ እርቅ ሊጠራ ይችላል ፣ ምህረት ወንም ይቅርታም ሊያደርግ ሁኔታው ይፈቅድለታል ደካማውንም አስገብቶ ቢፈልግ ያስረዋል ፣ ያንገላታዋል ፣ አስፈላጊም ሆኖ ካየው ለረፍቱ ሲል ትንሽ ግዛት ሰጥቶ በጋብቻና በመሳሰሉት ይተበትበዋል ፣ ወዘተ...

እኛ ተቃዋሚዎች ለወያኔ ሊያሣስበው ወይም ሊያስደነግጠው የሚችል ጥንካሬ ሳይኖረን ወደ እርቅ ሊያመጣው የሚያስችል ሁኔታ ሳንፈጥር በአቋራጭ እራሳችንን አንቱ ብለን የበላይነቱን እንደተቆጣጠርንና አዲስ አበባን እንደከበብን ይመስል እኛ ስልጣኑን ለብቻችን አንፈልግም ፣ እርቅ ይውረድ ፣ አብረን እንስራ ፣ ካልፈለክ መውጫ መንገድ እንከፍትልሀለን እያልን በራሳችን እናሾፋለን ፣ "ሲሉ ሰምታ ዶሮ ሞተች ከጭስ ገብታ" እንዲሉ ሁሉ ሲባል የሰማነውን ጥሪ መጮህ ትግሉን ወደ ወያኔ የመርዝ ጢስ ቤት (Gas Chamber) ለማስገባት መሮጥ ይሆናል ፡፡ ሐገራዊ እርቅ ከኃይል ሚዛን የሚነሳ ጥያቄ ነው ፡፡ ሐገራዊ እርቅ ማለት ለሐገር አንድነት ለኩልነትና ብልጽግና መንገድ ጠራጊ ብቻ ሳይሆን ያለውን መንግሥት በከንቱ ለማባበል የሚሰነዘር ባዶ መርሆ አይደለም ፣ ይልቅስ በዚህ እብሪተኛ በታኝ መንግስት በኢትዮጵያዊነታቸው በነጠላ ይሁን በአንድነት በጎሳ ይሁን በፖለቲካ እምነታቸው በሌላም ሌልም ለሰላምና ለዲሞክራሲ ሲሉ በሞት ለጠፉ ፣ ለታሰሩ ፣ ለተደበደቡና ፣ የአካልና የህሊና ዘላለማዊ ጉዳት ለደረሰባቸው ፣ በዚሁ ምክንያት ሀብት ንብረታቸውን ላጡ ፣ በዜግነታቸው ፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ለከፈሉት ስቃይና መከራ ይህ ሐቱራዊ እርቅ የነዚህን ሁሉ በደል መነሻና መድረሻ መርምሮ ከተደበቀበት የሚስጥር ጉድጓድ ሀቁን በማውጣት የተበደሉት ፍትህ ርትዕ (Compensation) የሚያገኙበትና በእውነትም ሐቱራዊ እርቁ እውነትን ያዘለ ተበዳዮች ወደ ሕዝባዊ እኩልነታቸው መብታቸውን አስከብሮ ወደ ሰላማዊ ኑሯቸው በመመለስ ቁስላቸው የሚሽርበትን እውነተኛ ሐገራዊ እርቅ የሚፈጠርበትን መንገድ ነው ፣ ይህ ሐቱራዊ እርቅ የተበደሉትን ማንሳት ብቻ ሳይሆን በዳዮችም እንደ ግፋቸው መጠን ለሰሩት ወንጀል በግል የሚጠየቁበትን ሁኔታ የሚያመቻች ለመሆኑ የማይታበል ነው ፡፡

እዚህ ላይ ማነው ይሄንን ጥያቄ እውነት የሚያደርገው? ጥያቄውስ በአሁኑ ሰዓት መገፋትም መምጣትም ያለበት ከማነው? የሚለውን ዋነኛ ነጥብ ላማንሳትና ተቃዋሚ ነን የሚሉ በዚህ ሰዓት ይህን ጥያቄ በማንሳት ትግሉንና ታጋዩን ሕዝብ ውዥንብር ውስጥ ከተውታል ፣ ስለሆነም አንድ የትግሬ ወይም የኦሮሞ ወይም

የአማራ ወዘተ… ተወላጅ ከሌላው ጋር በአንድ ጥያቄ ላይ አክርረው ሲከራከሩ ስለ ብሄራዊ እርቅ ስንል ይህንን እንተው በማለት በሄራዊ እርቅ ከዚህ ስለሚጀምር Paltalk ለ Paltalk ተቀራርበን እንስራ ይባላል ፡፡ ይህ የብሄራዊ እርቅ ጥያቄ ምን ያህል የተዛባና መሰረታዊ ይዘቱን እንዳጣ ያሳየናል ፡፡ በዚህ ላይም ድርጅቶች በበቂ ለሕዝቡ አለማስረዳታቸውንና ካድሬዎቻቸውንም አለማስተማራቸውን ያሳያል ፡፡

የዚህ ጉዳቱ በትግሉ ላይ እምነት ያላቸው ነገር ግን በተለያዩ ጥያቄዎች ላይ ግንዛቤአቸው ያልበሰለ ብዙሀን ለማንም አወናባጅ የተጋለጡ ያደርጋቸዋል ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም የወያኔን መንግሥት በተገቢው መሥመር ታግሎ ጥሎ እንዲሮጥ ማድረግ ወይም ተንበርክኮ ማሩኝ ለእግዚአብሄር እንዲል ከማረግ ፋንታ "ብሄራዊ እርቅ" በሚል ፈሊጥ ቆርጠን እንዳንታገል ዛሬ እርቅ ነገ እርቅ በሚል የላላ ወኔ የተበረዘ ሀሞት እንዲኖረን ተደርጓል ፡፡

"ብሄራዊ እርቅ" ከኃይል ሚዛን ጋር የሚነሳ ኃያል ነኝ ብሎ የሚያምነው ወይም ወደ ስልጥን የተቃረበ ለሰላም ለአንድነት ሲል የሚያነሳው የፖለቲካ ቅንነት የሐገራዊ አንድነትና የሐገር ግንባታ ጥሪ ነው ፡፡

በሐገራዊ እርቅ ስም ኃያሉ ደካማውን አስገብቶ እንደሚበላም አንርሳ ፣ ነገር ግን ይህ የርዕሳችን መነሻ አይደለም ለተከራካሪዎች ለማስገንዘብ ያህል እንጂ ፡፡

- ተቃዋሚ ድርጅቶች በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ምን መደረግ አለበት የሚለው በጊዜው ማጤንና ከሕዝቡ ቀድመው መገኘት አለባቸው ፡፡
- ተቃዋሚ ድርጅቶች የያዟቸው ድርጅቶች ከወሬና ፕሮፖጋንዳ ባለፈ ውስጣዊ ጥንካሬንና ውህደትን የአስተሳሰብ አንድነት መፍጠር አለባቸው ፡፡
- ተቃዋሚ ድርጅቶች ተበትኖ ያለውን የውስጥ ሆነ የውጭ ሐገር ያለውን ኢትዮጵያዊ ኃይል ወደትግል የሚቀላቀልበት ሐገራዊ ጥሪ ማሰማት አለባቸው ፡፡
- ተቃዋሚ ኃይሎች እስካሁን ቢያንስ ከምርጫው ወዲህ የወያኔ መንግሥት የሐገር ውስጥ ፖለቲካ ሁኔታና የተቃዋሚ ድርጅቶችን ገጽታ በቅጥ መርምረው በትግል አሰላለፋቸው ወደ ድል የሚወስደንን ጎዳና በመተለም መንገዱን ማጥራት ይኖርባቸዋል ፡፡

በነገራችን ላይ የቅንጅት የውጪው አካል በአንድነት እንደ አንድ ድርጅት ለመስራት መስማማታቸው ጥሩ እርምጃ ነው ፡፡ ይህ ብቻ ግን በቂ አይደለም የአስተሳሰብ አንድነት እንዲያዳብሩ የዓላማ ጥራት የትግል ወንድማማችነት ከምንጊዜም የበለጠ ይጠበቅባቸዋልና ጥሩ ጅምር ነው እንላለን ፡፡

በዚህ አንፃር ሁለት አብይ ነጥቦች ይነሳሉ ፣ ሀ) ለሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ ለመሳተፍ ያኮበኮቡና የቋመጡ እንደገና ሕዝቡን ተስፋ ለማስቆረጥ የሚዳክሩ ስለማይጠፉ የቀጠዩ ምርጫ ተሳታፊ ላለመሆን የጥያቄውን አንገብጋቢነት ከአሁኑ ማንሳትና አባሎቻቸውንና ሕዝቡን ማስተማር አቋማቸውንም ለምን? እንዴት? የሚለውን ሕዝቡን ለምን መሳተፍ እንደሌለብን ማስተማርና ማስረዳት አለባቸው እንላለን ፣ "ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" የትም አያደርስም ፡፡ ለ) አንደ (AFD) አይነት ጥያቄ ከኢትዮጵያዊነት አንፃር ሲታይ ትግሉን እንደጎዳው ፣ ይህም ቅንጅትንና አባሎቹን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የኢትዮጵያን አንድነት ለሚጠብቁ እንዳልጠቀመና በአንፃሩ ለኢትዮጵያ መኖር አለመኖር ደንታ ለሌላቸው እውቅና ከመስጠቱም በላይ ውስጣዊ ጥንካሬን በመስጠት ትግላችን ውዥንብር ውስጥ

እንደከተተው ተረድቶ ተሞክሮን መገምገም ይገባል ፣ በዚህ አንፃር ቅንጅት (AFD) ላይ የገባበትን ውስብስብ ችግር ተረድቶ አሁን አንድ ከሆኑልን ዘንዳ በዚህ በ(AFD) ዙሪያ ከገጠማቸው መሰናክል ለመላቀቅ ሳይውል ሳያድር እርምጃ መውሰድ ፣ ድሮ በመቃወም የራቁትን ሁሉ ለማሰባሰብ መርዳቱ ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ሊኖራቸው የሚገባው የኃይል አንድነት ያጠናክረዋል የልዩነቱንም ጎዳና በአዲስ መንፈስ ይከፍታል ።

የተቃዋሚው ኃይል ድርጅት በአንድነት የሚሰሩበትን የ(Material & Human Resource) ቸው የሚዳብርበት መንገድ መፍጠር መርዳት ይኖርበታል ።

የተቃዋሚው ኃይልና ድርጅት ባለው ከፋፋይና በታኝ የወያኔ መንግሥት ላይ ግልፅ የሆነ አቋም ሲኖራቸው በዓለም አቀፍ ማህበር ላይ ተፅእኖ ማድረግ ይችላሉ ።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ድርጊቶች ሲሟሉና ግልፅነት ሲኖረን የተቃዋሚ ድርጅቶችና በነሱ ስርም የተሰበሰቡት ሕዝባዊ ወገኖች ኃይል ያገኛሉ የወያኔ መንግሥት መዳከሙ የማይቀር ይሆናል ፣ ያን ጊዜ ነው እየተዳከመ ሲሄድ መሠረቱ ሲናድ መፍረክረክ ሲጀምር ወደ ሐገራዊ እርቅ የሚመጣው ።

- ያን ጊዜ ነው እኛም ተጠናክረን ሥራችን በሐገር ውስጥ ምመሰረት ሲይዝ ባሉን ድርጅቶች መዋቅርና መረብ ስንተማመን ኃይላችን መጎልበቱን ስናረጋግጥ ወያኔ በግድያና በእስር ሊፈታው አለመቻሉ አዋጅ ሲሆን የሐገራዊ እርቅ የሚለውን ብናነሳ ለጠሪውም ለተጠሪውም ትርጉም የሚሰጠው ።
- ያን ጊዜ ነው እነዚህ ተቃዋሚ የሚባሉት ጩኸት ብቻ ሳይሆን መሠረት አላቸው ፣ ድርጅት አላቸው ብሎ አቶ ስብሀት ነጋ ከምህረት ጥሪ ወደ ሐገራዊ እርቅ ሳይወድ በግድ የሚያዘነብለው ።
- ያን ጊዜ ነው ወያኔ ተቃዋሚው በውነት ተጠናክሯል ብሎ ወደ ኤርትራ ወይም ዚምባዌ ከመንግስቱ ጉርብትና የሚጠይቀው ።

የወያኔ መንግሥት በታኝ አምባገነን ነው ፀረ ሕዝብና ፀረ ዲሞክራሲ ስንል በርግጥ በፖለቲካ በይዘቱ ፣ በተግባሩ ፣ በአመለካከቱ ፣ በአደረጃጀቱ በርግጥ ከላይ የተዘረዘሩትን አሉታዊ ገጽታዎችን የያዘ ነው? ወይስ ዝም ብለን ለመጥፎ መንግሥት የሚሠጠው አባባል ሰምተን በመለጠፍ የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው?

እውነተኛ ታጋዮች የሕዝብን መጨቆን የተገነዘቡ የዲሞክራሲን መታሰር የተረዱ የአገርን መቆራረጥ ጅምሩን ያዩና ሂደቱን ያጤኑ ሀላፊነት የተሞላው መንግሥት ምን እንደሆነ የተመለከቱ የወያኔን እብሪተኛና አምባገነንነትን ትምክህተኛ ሕዝብን ከፋፋይና ለኢትዮጵያ ሐገራችንና በአንድነት ለሚያምነው ሕዝባችን ነቀርሳ እንደሆነ የተቃዋሚ ድርጅቶችም ታጋይ ወገናችንም ጠንቅቆ ያውቃል ብለን እንገምታለን ።

ታዲያ እብሪተኛ ፣ ትምክህተኛ ፣ አምባገነን እያልን ታረቀን ፣ ተማለደን ስንል የአምባገነንነቱን ጠባይ ረስተነው ነው? የተቃዋሚ ድርጅቶችንና አባሎቻቸውን ፣ መሪዎቻቸውን ከስልጣን መያዙ በፊትም በኋላም ሲያስር ሲገድል የሕዝቡን ድምፅ እየረገጠ አሁንም የሐገር ከኀዲዎች በማለት የድርጅት መሪዎችን በእስር በሚያሰቃይበትና የተቃዋሚው ህልውናን በንቀት አክ-እንቱፍ ብሎ በዘጋበት ወቅት ተቃዋሚ ድርጅቶች አገር ቤት አመራር መስጠት አቃተን ብለው የፀጥታውን ኃይል እያወገዙ ዞር ብሎ እርቅ እያሉ ጥያቄ የፖለቲካ ትግል ሳይሆን በቀላሉ ጠላትን አለመረዳትና የሚሉትንም አለማወቅ የዘልማድ ፖለቲካ ይሆናል ፣ ከዚያም በመለስ የፖለቲካ ትግል ሳይሆን የፖለቲካ ልመና ይሆናል ። ከዚህ ባለፈ መተቸት

ማክረር ስለሚሆን ድርጅቶች ይህን የመሳሰሉትን መርኋቸውን በቅጡ መርምረው በወያኔ ጠላታችን ላይ የጠራ አመለካከት መያዝ ወቅታዊና አንገብጋቢ ጥያቄ ይሆናል ።

ግልጽ ሆኖ ጥርሱን አግጥጦ በመጣው ጠላት ላይ የተዋቀረና የተጠናከረ ድርጅት ሳይኖረን ብሄራዊ እርቅ ጥያቄ ማንሳት ከፈረሱ በፊት ጋሪውን ማስቀደም ለመሆኑ ጥያቄ የለውም ።

በ97 ምርጫ ተቃዋሚ ድርጅቶች ወያኔን በድምጽ ድባቅ መምታታቸው የድርጅቶችን ጠንካራነትና ዘላቂ ድርጅታዊ መዋቅር ይዘት ያለው ሥራ እንዳላቸው አላስመሰከረም ፤ ከምርጫው በኋላ ወያኔ ከላይ ያሉትን መሪዎች ሲያስርና ከፊሎቹም ከወያኔ ሲዛመዱ ቀጣይና ተከራካሪ ትግሉንም ሐገር ውስጥ የሚመራ መዋቅርም ድርጅትም እንደጠፋ የማንደብቀው ሀቅ ነው ። እንዳልነው የምርጫው ውጤት ሕዝቡ በወያኔ ምን ያህል ጥላቻ እንዳለው አሳይቷል ፤ ስለሆነም በአማራጭነት የቀረቡለትን ቅንጅትን ፤ ሕብረትን ተቀብሏል ፤ ምንም እንኳን ልደቱና ጓደኞቹ ከቅንጅት በየነና መራራ ከነጀሌያቸው ሕዝቡ የሰጣቸውን አደራ በልተው ከወያኔ ጋር ቢዘምሩም ዞሮ ዞሮ ቅንጅትም ሆነ ሕብረት በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ድርጅታዊ ሥራ በበቂ እንዳልነበራቸው ገሀድ ሆኗል ።

ስለዚህም ነው አሁን ተመልሰን ከከንቱ መመፃደቅ ወጥተን ድርጅቶቻችንን ለመገንባት ሕዝቡንም ለዘላቂ ትግል እንዲሰለፍ መሥራት ያለብን ፤ ይህን በመሰለ የተጠናከረና ሕዝቡን በትግል ድርጅት መዋቅር ያላቀፈ እስከሆነ ድረስ ያለን ፖለቲካ የገበያተኛ ፖለቲካ ይሆናልና እንደ ግራዋ እንጨት ጢስ በቅጡ ሳይነድ ቦግ እልም እያለ ፋይዳ ሳይሰራ ጨሶ ያልቃል ።

የአዲስ አበባ ተማሪዎች ዛሬ ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ ፤ እስታዲዮም ውስጥ ሁለት ጣት አሳዩ ፤ የኢሓፓ መዝሙር ሲሰማ ሕዝቡ ተላቀሰ ፤ ይህ ሁሉ የሕዝቡን ምሬትና ለትግል ዝግጁነቱን እንጂ የድርጅቶችን ጠንካራነት አያሳይም ። እንዲያውም ደካማነታቸውን እንጂ ።

የሐገራዊ እርቅ ጥያቄ አሁን የመነሻው ጊዜ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ያለቦታውና ያለጊዜው የተነሳ ከመሆኑም ሌላ የጠላትን መሰረታዊ ፀባይና ማንነት አለመገንዘባችንንም ለማሳየት ጭምር ነው ፤ በምን ወቅት የተቃዋሚ ድርጅቶች ያነሱታል የሚለውንም ጥያቄ እንድንመረምር ይረዳናል ብለን እናምናለን ። የዚህ ጥያቄ አንደኛው ፀባዩ ኢትዮጵያ ሐገሬ በሚሉ ኢትዮጵያውያን መካከል የሚነሳ ጥያቄ ነው!

በማጠቃለያው የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ ያገባናል ለሚሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲወያዩበት እንጋብዛለን ። ገንቢና ትምህርታዊ የሆነ ጥናትና ጽሑፍ ከድርጅቶችና ከምሁራን ኢትዮጵያውያን እንጠብቃለን ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ከምንተስኖት ሲራክ